# የ"ግንቦት ሰባት" ግብፅ ሜድ— ምን ለሚሄድ?

❖ "እባብ የልቡን ዓይቶ እግር ነሳው"

ሀገርኛ ይትብሃል

ሸረፋ ከድር

ksherefa@gmail.com

ከየት እንደ ምጀምርና ምን እንደምል እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ሀገሩን ለሟሸጥ የሚያስማማ ከንቱ ተላላኪ ዳግማዊ ቅሌትን በአይጋ ፎረም ድረ-ገፅ ላይ ከማነንበቻው ሳነብና እንዲህ ዓይነቱ 'ኢትዮጵያዊ' መኖሩን ስሰማ ቃላት አቅመ ቢስ ሆኑብኝ፡፡ ጣቶቼም ብርክ ያዛቸው፡፡ ለጆሮ ሰቅጣጭ ዜና በመሆኑ — ብዕሬም አፈረች፡፡ የ"ዶክተር ኢኮኖሚስት" ተብዬወን ነወረኝነት የሚያጋልጡ ቃላት እያደንኩ ጊዜ ከማክከን፣ እንዲያው አደባባይ ወጥቼ በለፈፍኩት እመርጥ ነበር። ንዴት ለሰው ሲያካፍሉት ይቀል የለ?!...አዎ! እንዲያ ነው።...

በእርግጥ አሁንም እየጮኩ ነው፡፡ ይህ የምታዩት ወረቀት እንደ አደባባይ ቢቆጠርልኝና ብዕሬም እንደ ጡሩንባ ብትወከልልኝ፡፡ አሊያም የሀገር ከሃዲዎችን እኩይ ድርጊት እያየች እያነባች እንደሆነ ተደርጎም ቢሆን ይተርጎምልኝ፡፡ እናም እነሆ በአሸባሪው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነወረኝነት የተሸማቀቀው ኢትዮጵያዊ ማንነቴን በብዕሬ በኩል ለመተንፈስ እየሞከርኩኝ ነው፡፡ የዶክተር ተብዬወን ሀፍረት ምግባር ኢትዮጵያ እንድታደምጥበት፤ አድምጣም እንድታፍርባቸው— እንድታፍርላቸው፣ እንድታዝንባቸው ተመኘሁ— የሚይበጃት ይፈር፣ ይዘንና!

"የአሁኑ ይባስ" ይላል ታታሪው የሀገሬ አርሶ አደር— ቀደም ካለው ጉዳይ እጅግ አሳፋሪ ወይም አስገራሚ ጉዳይ ሲገጥመው፡፡ እርግጥም አሸባሪው "ዶክተር ኢኮኖሚስት" ለይቅርታ የሚይመች ታሪካዊ ስህተት ፈጽመዋል፡፡ ለባዕድ አሳልፈው ሸጠውናልና አብረን እንወቀሳቸው፣ ወግዝ ከሙአርዮስ እንበላቸው፡፡ ባንዳዎች የሚከማ ልቦና ባይኖራቸውም ሚከስ መቅለላቸውን እንንገራቸው፡፡ ወድ አንባቢዎቼ ጫፊጥ ወዳለው ጉዳዬ ገባሁ ማለኝ...ይቅርታ እጠይቃለሁ!... እያወጋሁ ያለሁት ስለ ግንቦት ሰባቱ የሽብር ቡድን ፊታውራሪ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ እና ስለ ባንዳው ድርጅታቸው ነው፡፡

እርግጥ አይጋ ፎረም ድረ-ገፅ "ግንቦት ሰባት ዲ" የተሰኘን የግንቦት ሰባት ግንጣይ ቡድንን በመጥቀስ ከሰሞኑ የሽብር ድርጅቱ ሜሬ ተብዬዎች ግብፅ ወስጥ በሮ ለማካፈት ደፋ ቀና እያሉ ማሆኑን ያነበበ ሰው፤ የእኔ ዓይነት ስሜት እንደሚከማው አልጠራጠርም። ምክንያቱም የጥፋት ድርጅቱ ዋነኛ ተልዕኮ የሀገራችን ህዝቦች በከፍተኛ የተነሳሽነት ግለት እያከናወኑት ካለው ከታላቁ የህዳሴ ግድብ ልማታዊ ስራ ጋር ሊያያዝ የሚችል በማሆኑ ነው። ያም ሆነ ይህ ግን "የግንቦት ሰባት ግብፅ ሜድ—ምን ለሚሄድ?"

የሚል ጥያቄን ስናነሳ፤ የሽብር ቡድኑን ሙሁ አሳፋሪ ማንነት እንዲሁም የድርጅት ተብዬውን የለየለትን ሀገርን ከጀርባ በጦር የመውጋት ተግባርን በይፋ ስለሚያመላክተን ነው።

አዎ! ከአሻባሪው ዶክተር ብርሃኑ ምን ሚልካም ነገር ይገኛል የሚሉኝ እልፎች እንደሚሆኑ እገምታለሁ፡፡ ትክክል ናቸው፡፡ እኔም እያወራሁ ያለሁት ሚልካምነታቸውን ሳይሆን ቅሌታቸውን ነው– በኢኮኖሚክስ ዲግሪያቸው አስልተው ቀደም ሲል ለአስሜራው "የሁከት ንጉስ" አሁን ደግሞ የህዳሴው ግድብ ፀር በማሆን ሀገርን ለማሻጥ ያዘጋጁትን ሰነዳቸውን ወይም የሃራጅ ወረቀታቸውን፡፡...እናንተዬ ምንኛ የሚረ ትንሽነት ነው ጃል!... የምር የሰወዬውን ሰሞነኛ ነገር ሥራ ሳወጠነጥን የመሆንን፣ የዕድሜና ሰው የመሆንን ዋጋ ዜሮ ያደርግብኛል፡፡ ተምረው ለሀገርና ለወገን በርካታ ስራዎችን ያከናወኑ የሀገር ወሮታ ከፋይ ምሁራን ያሉትን ያህል፤ በዚያው ልክ ጥቂት ለሆዳቸው እንጂ ለወገንና ለሀገር ያልቆሙ አሜሪካ አሊያም የሚላላከብት ሀገር ወስጥ ሆነው የሀገር ቤት ሁከት የሚፈታቸው መኖራቸው አልቀረም። እንደ እወነቱ ከሆነ እዚህ ላይ ሸብተው አሊያም ተሚልጠው ዲግሪዎችን የሰበሰቡ ሁሉ፤ ከአሜልዕክቶች እንደ አንዱ ቅን፣ ሃቀኛ፣ አዋቂ፣ ብልህ፣ ሆደ ሰፊ... የሚምስሉኝ ማሞ ቂሎ ነኝ እያልኩ ግን አይደለም፡ ፡ ሆኖም በየትኛወም ሚዛን ብመዝነው ሀገሩን ለጠላት የሚሸጥ ሆድ አደር "ምሁርና ሽማግሌ" ይኖራል ብዬ በህልሜም በእወኔም ገምቼ አላወቅም፡፡... ለዚህም ነው ብዕሬ እንዲህ የሚረቸው።

እርግጥ የግለሰቡ የትላንት ዳራ ሲበረበር ስብዕናቸውን ጥያቄ ወስጥ የሚያስገቡ ሃቆች ይገኛሉ፡፡ በትረ ስልጣን የሚያስገኝልኝ ከሆነ ከዲያቢሎስ ጋርም በሽርክና የማስራት ችግር የለብኝም ብለው ነበር — አሜሪካ ቁጭ ብለው ስልጣን እንደ እህል ወሃ የሚርባቸውና የሚጠማቸው አሸባሪው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፡፡ ከትላንት እስከ ዛሬ ድረስ የኤርትራ መንግስት ተላላኪና ተወርዋሪ ድንጋይ በማሆን ተንቀሳቅሰው አንዳችም ፋይዳ ያላስገኙት አሸባሪው ሰወዬ፤ ዛሬ ደግሞ በአዲስ ሚልክ ስራ ጀምረናል ለማለት በቀበፀ–ተስፋ ካይሮ ላይ ቢሮ ከፍተው ዳግማዊ ሀገራዊ ክህደታቸውን ሊሰዩን እየተሯሯጡ ናቸው። እርግጥም አሁንም ቃላቸውን አልበሉም፡፡ በኢትዮጵያ ላይ ትላንት ያልተሳካውን "መፃረካዊ አካሄድ" ለማስቀጠል ይፈልጋል እየተባለ በበርካታ ፀሐፍት ከሚታቸው ከአዲሱ የግብጽ ጋር በትብብር ለማስራት ደፋ ቀና እያሉ ነው፡፡ ሀገራቸውን ለማሻጥ እየተደራደሩ ነው፡፡...ምንም እንኳን አንድም ነገር ሚፈየድ ባይችሉም።

ለነገሩ ሰወዬው ፍፁም ፀረ– ኢትዮጵያዊ በማሆናቸው የሰሞነኛ አሳፋሪ ምግባራቸውም የተለሚደ የባንዳነቱ ተቀፅላ እንጂ አዲስ ጉዳይ አይደለም፡፡ አሸባሪው ዶክተር ቀደም ሲልም ከዋህቢያና ከስደተኛው ሲኖዳስ ጋር በማሻረክ ኢትዮጵያዊያንን በሃይማኖት ሰበብ ለማበላላትና ኤኬልዳማ ለሚድረግ ተወገርግሯል፡፡ በህዝብና በመንግስት ቅንጅታዊ ተግባር ስዕለቱ አልይዝ እያለባቸው እንጂ፤ እንደ እርሳቸው የቀን ቅዠት ቢሆንማ ሀገራችን እንዳልነበረች በሆነች ነበር፡፡

በነገራችን ላይ ከግብጽ ጋር በትብብር ለማስራት ደጅ እየጠና ያለው የዶክተር ብርሃኑ ነጋ የጥፋት ክለብ ግንቦት ሰባት ብቻ አይደለም፡፡ የሽብርን ጥበብ ያጠምቁትና ሰይጣንነትን ያሰለጡት አቶ

ኢሳያስም ቢሆኑ በአማካሪያቸው አቶ የማ ገብረአብ እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ኡስማን ሳላህ አማካኝነት ለግብጽ ጦሯ ልኳል — የአብረን እንስራ ሚልዕክት፡፡ ጥይት ሲተኮስ ካልሰማ አሊያም የጥይት አረር ካልሸተተው ሰውነቱ ቆፈን እንደያዘው ሰው የሚንቀጠቀጠው የአስመራው የሽብር አጋፋሪ ቡድን ፤ ግብጽን ብቸኛ የናይል ወንዝ ተጠቃሚ የሚያደርጋትን ነባሩን ህግ እንደሚደግፍ ለፕሬዝዳንት ሞሃመድ ሞርሲ ገልጿል፡፡ አይደለም። በሌላ አባባል የህዳሴውን ግድብ ግንባታ እየታቃወመ መሆኑ ነው— በማያገባው ጉዳይ እንደ እርጎ ዝንብ ጥልቅ በማለት። ዳሩ ግን የኤርትራ መንግስት በተፋሰሱ ሀገራት ውስጥ ያለው ቦታ ታዛቢነት ነው። እናም አንድም ጠብታ ውሃ ለናይል ወንዝ ሳያዋጣ ስለ ግብፅ ታሪካዊ የውሃ ባለቤትነት መቀበጣጠሩ— የተለመደው "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" የሚለው አሮጌ የዲፕሎማሲ ስልቱ ከመሆን የዘለለ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም።

ለነገሩ የአቶ ኢሳያስ መንግስት ሚፈራገጥ ለመላላጥ እንጂ ትርጉም አልባ ነገር አይፈጥርም። እናም ወደ አማዙሩ ሽብርተኛ እንመለስ— ወደ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፡፡ ዶክተሩ ጫልጥ ያለ የሻዕቢያ አድናቂና ቋሚ ሚልዕክተኛ ነው፡፡ ምናልባት ሰሞኑን ግብጽ የተገናኙት ያሳለፏቸውን ምርጥ የሽብር ዓመታት ዳግም በትዝታ እያጣጣሙ ፀረ – ኢትዮጵያ አጀንዳ ሊነድፉ ይሆናል፡፡

ሰወዬው በአስመራ መንግስት ድጋፍ በርካታ የጥፋት ጥመኞችን አሰልጥኖ ወይም አሰይጥኖ ሀገራችን ወስጥ ሁከት ለመፍጠር የአቅሚቷን ያህል መሯሯጣቸው አይዘነጋም፡፡ ምንም እንኳን ጀሌዎቻቸው የንፀሃንን ደም ለማፍሰስ የመቋመጣቸውን ያህል፣ ደም ሳያፈሱ እየታፈሱ ወደ ማረሚያ ቤት ወረዱ እንጂ። ይሸብር ቡድኑ አንድ ጊዜ ከሻዕቢያ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከዋህቢያና ከስደተኛው ሲኖዶስ ጋር ለፀረ – ኢትዮጵያ ትግሉ አብረውት እንዲሰሙሩና ታግለው እንዲያታግሉት በብልጣ ብልጥነት ሲክለበለብ የነበረ ቡችላ የጥፋት ሃይል ነው። እንግዲህ የሃፍረተ ምግባሮቹን ቁጥር ከፍ ለማድረግና መቼም የማይሰበር የነወር ሪከርድ ለማስመዝገብ ከኤርትራው የጥፋት አባቱ ጋር ተቀጣጥሮ ነው—ካይሮ ላይ የተገናኘው ማለት ይቻላል፡፡

ነገርዬው "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" ሳይሆን አይቀርም፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ግብጽ ጠላታችን ናት እያልኩ አይደለም፡፡ ልትሆንም አትችልም። የግብፅ ህዝብም ይሁን አዲሱ የግብፅ መንግስት ተባብሮ በመደግ የሚያምን ነው። ከተፋሰሱ ሀገራት ጋር በጋራ ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውን በየጊዜው እየገለፁ ነው። በእኔ እምነት አንድ ያገጠጠ ሃቅ ይታየኛል፡፡ ይኸውም ከተለያዩ የመፃረክ ዘመን ቅሪት ባለስልጣኖቿ ተዘዋዋሪና ቀጥተኛ አስተያየት እንደምንሰማው ግብጽ በአባይ ወንዝ የመጠቀም መብታችንን እንደማታከብር ነው፡፡ ይህ ደግሞ የቀድሞዎቹ የግብፅ ገዥዎች አማላካከት ነው—ትናንትና ተሞክሮ ያልሰራ።

ዛሬ ግን ትላንት አይደለም፡፡ በዛሬዋ ግብፅ እነ ቡጥሮስ ቡጥሮስ ጋሊ፣ ገማል አብዱል ናስር፣ እነ ሆስኒ መፃረክ የሉም፡፡ ከአሮጌ አስተሳሰባቸው ጋር ተሰናብተዋል፡፡ እነርሱ ግብጽ የአባይ ወንዝ ብቸኛ ባለይዞታና ተጠቃሚ መሆኗን አስለተው ለግብጽዊያን የሰበኩ የትላንት ባላንጣዎቻችን ናቸው፡፡ ይህ ማለት ግን አዲሱ የፕሬዚዳንት አህመድ ሞርሲ አስተዳደር የህዳሴውን ግድባችንን በፍጹም ደስታ ይቀበለዋል

ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም አንድም ለበርካታ ትውልድ የተሰበከን ጭፍን ፖለቲካ በቀላሉ ማናድ ስለሚከብድ፣ ሁለትም በከንቱ ጥርጣሬ በአባይ የመጠቀም መብታችንን በይፋ ባይቃወማም ከፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች ጋር እያደረገ ያለው አዲስ የግንኙነት አቅጣጫ የሚያመላክተን ጉዳይ በመኖሩ ነው፡፡

ያም ሆነ ይህ በአዲሱ መንግስት በኩል የሚቅማማት አዝማሚያ ቢስተዋል አይገርምም፡፡ ለዘመናት የተገነባን አስተሳሰብ በአንድ ሌሊት መቅረፍ ይከብዳል፡፡ እናም የሙርሲ መንግስት አቅማማ ማለት በጠላትነት ተሰለፈ ማለት አይደለም፡፡ ለወጥን በቶሎ አለመቀበል ተፈጥሮአዊ መሆኑንም ማዝንጋት የለብንምና፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዚያች ሀገር ስልጣን የተረከበው አዲሱ አስተዳደር ከሙባረክና ከድህረ-ሙባረክ ዘመናት ጋር ሲነጻጸር በናይል አጠቃቀም ዙሪያ ያለው አንድምታ እየተቀየረ መጥቷል፡፡ የህዳሴው ግድብ ግንባታ የየትኛወም የናይል ተፋሰስ ሀገር ጥቅም የሚጎነካ ነው። ሀገራችንም ይህን ሃቅ በተጨባጭ ሳይንሳዊ ማስረጃዎች አስደግፋ ለማስረዳትና አሮጌውን አስተሳሰብ ቢያንስ ለማሻርሸር በመቻሏ፤ የሁለቱ ሀገሮች ግንኙነት አሉታዊ ለወጥ እየታየበት ነው፡፡ በዚህም ሳቢያ ከግብጽ ጋር ያለን ግንኙነት በኢንቨስትመንት፣ በባህል፣ በግንድና በዲፕሎማሲ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ እናም ምናልባትም ግንቦት ሰባት በካይሮ ቢሮ ለመክፈት እንዲሁም የቀጣናው አሸባሪ የሆነው የኤርትራ መንግስት የጠላትነት አቋም ለግብፅ መንግስት የሚፈይደው አንዳችም ነገር የለም።

ለነገሩ አባይን ለማጠቀም ደፋ ቀና ማለታችን የሚያስከርፋቸው ወገኖች አይኖሩም ማለት አይቻልም፡ ግብጽን የሚወክሉ ባይሆኑም ግር ግር ለሌባ ይመቻልና አጋጣሚውን ተጠቅመው ፀረ - ኢትዮጵያዊነትን ለማቀንቀን የሚያማትሩ ግለሰቦች አሉ፡፡ ለአብነት ያህል የኢትዮጵያ ሙስሊሞቸ እንደተበደሉ በማስመሰል ፀረ - ኢትዮጵያዊነት እንዲፋፋም ጥሪ ያቀረቡትን ግብጻዊ- አሜሪካዊ የሆኑትንና የሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ አቀንቃኝ የሆኑትን የሼክ ሻከር አልሳይድን ጃሃዳዊ ጥሪ ማስታወስ ይቻላል፡፡ እርግጥ የሰወዬው የጅሃድ ጥሪ የግብፅ አቋም አለመሆኑን ሀገሪቱ አሳወቃለች፡፡

ዳሩ ግን የግብጽ ምላሽ አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ በአባይ ወንዝ የማጠቀም መብታችንን የሚፍግ አንዳች ህግም ይሁን ኃይል ከፀሃይ በታች የሌለ መሆኑ ማታወቅ ይኖርበታል ባይ ነኝ። የህዳሴው ግድብ ግንባታ መላው ኢትዮጵያዊ አሻራ ያረፈበት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ግድቡን የደገፈው በሞራል ብቻ አይደለም፡፡ በጉልብቱም፣ በዕውቀቱም፣ በገንዘቡም በፀሎቱም ጭምር ነው፡፡ የሰው ስጋና ደም ለግንባታው የሚያገለግል ቢሆን ኖሮ፣ ይህን በመካወን ግድቡን ለማስለጥ የተዘጋጁ እልፍ ናቸው ብል እንደሚጎነን የሚቆጠርብኝ አይመስለኝም፡፡

የህዳሴው ግድብ ግንባታ አንድነታችንን ይበልጥ ያጠበቀ ነው፡፡ መቻልን የቻልንበት፣ አንድ ከሆንንና ከተባበርን የማንወጣው ፈተና አለመኖሩን ያየንበትም ይሁን ያሳየንበት ጭምር ነው — ለወዳጆቻችንም፣ ለጠላቶቻችንም፡፡ የህዳሴው ግድብ በሥነ - ልቦናዊ ድል እሴትነት ብቻ ተመንዝሮ የሚለካ አይደለም፡፡ በአባይ ወንዝ ዝንተ-ዓለም ማጠቀም የማንችል አቅሙ ቢስ የበይ ተመልካች አድረገው

የሚቆጥሩንን ሁሉ ኩም አድርገንበታል፡፡ ግና ምናልባትም "ይህች ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም" የሚሉም አይታጡም፡፡ እናም ግብፅን ተጠልለው 'ዘፈንሽ ዘፈኔን፣ ዜማሽ ዜማዬን' አብረው ለማቀንቀን የሚቋምጡ ፀረ – ኢትዮጵያዊያን ሃይሎች ወደ ካይሮ ቢያቀኑ አይገርምም፡፡ ልክ እንደ ኢትዮጵያዊ ተብዬው ባንዳ— እንደ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፡፡ አዎ! ተስፋ ሰጪዎን ጉዟችንን ሲያስተወሉ "ምነው ቀድሜ በሞትኩት" በሚሉት ዳግማዊ ሞታቸውን የሚሞቱ የአስተሳሰብ አሮጌዎች ግብጽን እንደ ምቹ መደላደል አድርገው በመቁጠር ማምዙራቸው አልቀረም— የሚያዋጣ ስሌት ባይሆንም፡፡

ያም ሆነ ይህ የዘመኑ ግብፃዊና አዲሱ መንግስት ጠላታችን ባይሆንም፤ የዶክተር ብርሃኑ ነጋ አስላለፍ ግን የለየለት ባንዳነት ነው፡፡ ወደ ካይሮ ያቀኑት ግብጽ የኢትዮጵያ ጠላት እንደሆነች አድርጎ ቀምሮ ነውና ሀገርን ሸጧል፡፡ ግና በሁለት ምክንያቶች ይህ እኩይ ባንዳዊ እሳቤያቸው የሚሰራላቸው አይመስለኝም። ምክንያቱም አንደም የዛሬይቷ ኢትዮጵያ የትላንቷ ባለመሆኗ፤ ሁለትም ዓለም በአንድ መንደር በምትመስልበት በዘመነ ግሎባላይዜሽን ሚሪቁንም ሆነ አጥንቱን ለእኔ ባይ ስግብግብነት ቦታ ስለሌለው ነው። ይህ ነወረኛ ተግባሩም "ሁሉንም ትመኛለህ፣ ሁሉንም ታጣለህ" የሚባለው የዜሮ ድምር ፖለቲካ ስሌት በመሆኑም የሚከካ አይደለም። እናም አዲሲቷ ግብፅ እንደ ጥንቱ አባይ የብቻዬ ነው የሚል አቋምን በመንግስት ደረጃ አፊሴላዊ በሆነ መንገድ ባታንቀባርቅም ቅሉ፣ የዶክተር ብርሃኑ ቅዥት ግን ይህን እንድትል ያለመ በመሆኑ ይፋዊ ሀገር ክህደት ነው፡፡ ሀገሩን የካደ ደግሞ ባንዳ ሆኖ ልስራልህ የሚለውን አካል ያለመካዱ እርግጠኛ መሆን ስለሚያቻል በሌላው ወገንም ቢሆን ተዓሚኒ ሊሆን አይችልም።

እናም በእኔ እምነት የሰውዬው አካሄድ ኢትዮጵያን በጥቁር ገበያ ከመቸርቸር የሚያተናነስ የጥፋቶች ሁሉ ጥፋት ነው፡፡ በታሪክም በህግም የሚያስጠይቅ፡፡ ከ80 ሚሊዮን በላይ ህዝብን ዘርግቶ የመሸጥ ያህል የሚቆጠር ነው፡፡ ባህላችንን፣ እሴቶቻችንን እንዲሁም የአበውንና የእመውን የሀገር ፍቅር ታሪክን ብሎም ዛሬ ላይ በልዩነት ውስጥ ያለውን የአንድነታችንን ወርቃማ እውነት አርክሰዋል፡፡… አቤት የስልጣን ጥማትና እራብ ፣ አቤት የስልጣን ሱስ!... እውነቱን ነው የሀገሬ ሰው "እባብ የልቡን አይቶ እግር ነሳው" የሚለው— እባብ እንደልቡ ተሯሩጦ ለመንደፍ እግር በማጣቱ እንጂ በልቡ የትየለሌ የጥፋት ዕቅዶች መኖራቸውን ለመግለጽ ሲፈልግ፡፡ እነ ግንቦት ሰባት አቅመ ቢስ መሆናቸው በጀ እንጂ እንደ ልባቸው ሞኞት ቢሆን ኖሮ፤ በሽብር መርዛቸው ሀገራችንንና ህዝቦቿን ከሰላም፣ ከልማትና ከዴሞክራሲ ግስጋሴያቸው ወደ ኋላ ባሰቀሩ ነበር፡፡ ታዲያ ምን ያደርጋል?!—ሴራቸው ሁሉ በነበር ቀረ እንጂ። …እውነትም "እባብ የልቡን ዓይቶ እግር ነሳው"…

ታዲያ እኔም እላለሁ— ዶክተር ብርሃኑን የልባቸውን አይቶ አቅም ነሳቸው፡፡ ለጥቆም ስልጣንን ነሳቸው። ከዚያም የሽብር ዛር ሰፈረባቸው። ከሻዕቢያ ጋርም አቆራኛቸው። አሜሪካ ሆነው የሽብር ሽምጥ ፈረስ ጋላቢ አደረጋቸው… አዎ! ሰውዬው ሃሳብ እኩይ ነው— ምግባረ ትንሽ፡፡ የክፋታቸውን ግዝፈት በተመለከተ አንድ ፀሐፊ እንዳለው አካሄዳቸው ሰይጣናዊነት ነው፡፡ አጭዶ የሚያደንዝ የሽብር ማጭድን

ታጥቀዋል። በእኔ እምነት ሀገር ከሚካድና ህዝብን ባንዳ ሆኖ ከመሸጥ የሚከረ ስህተት የለም፡ ማንነትን መካድ ከመኖር በታች ይመስለኛል፡፡ አጉል መሆን ነው ፡፡ መካሸፍ። ከምንም ሆነ ከህያው ፍጡራን በታች፡፡ ለነገሩ ሰውዬው ከተማቸው እንኳንስ ግብጽ ቀርቶ ሌላ ቦታም ቢሄዱ፤ እኔ በግሌ አይሞቀኝም፤ አይበርደኝም፡ ግና አንድ ጥያቄ አለኝ፡፡ እርሱም 'ሰውዬውን ይህን አይነት ባንዳነት ከወዴት አገኛቸው?' የሚል ነው።... በደምና በዘር ሃረግ እንዳይባል ማንነታቸው የሚቀዳው ከወደ ኢትዮጵያ ነው—በማንነታቸው ጉዳይ ለድርድር ከሚቀርቡት አበውና እመው፡ ከታሪክ ኮረጇም እንዳይባል እመውና አበው በብሔራዊ ጥቅም ጉዳይ አንገታቸውን ለሰይፍ የሰጡ ብሎም ለማዝባቸው ያደሩ ናቸው። እናስ "ዶክተር ኢኮኖሚስቱ" የየት ሀገር ባንዳ ናቸው እንበል?..ወፍ ዘራሽ ወይስ ሌላ?...

...የምን ወፍ ዘራሽነት ነው፡ የሰውዬውን የትውልድ እንክርዳድነት ለማየት የዘመነ - አድዋ ኢትዮጵያዊንን እናስታውስ፡፡ ደግ የሰራ በደግ መሳሳቱ አይቀርምና። ታዲያ ያኔ በዘመኑ ኢትዮጵያዊያን በወስጥ ጉዳይ የሚያግባቡባቸው አጀንዳዎች ነበሯቸው፡ ፖለቲካዊ ልዩነት ልንለው እንችላለን፡፡ በግዛት ይገባኛል ጥያቄም ቅራኔዎች ነበሩ፡፡ ለፀረ - ጣሊያን ወረራ ክተት በተባለ ጊዜ ግን፤ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ልዩነቱን ወዲያ አሽቀንጥሮ ነበር በአንድነት የተሰለፈው— የቀረው ይቀራል እንጂ በኢትዮጵያዊነትና በብሔዊነት ጥቅም ድርድር የለም ነበር ያለው፡ የትናንት ታሪካችን ወርደም ሆነ ጥልቀቱ በለካ በአንድነት ጉዳይ የሚዝነፍ አልነበረም፡ የጣሊያን አገልጋይ ተደረገው ይቆጠሩ የነበሩና በዘመኑ አጠራር 'ባንዳ' የሚባሉት ሳይቀሩ እንኳን፤ የቁርጥ ቀን ሲመጣ ጣሊያንን 'አፍንጫህን ላስ' ነበር ያሉት፡፡

አዎ! የእናት የአባቶቻችን እንዲሁም የቅድመ አያቶቻችን ገድል ሲገለጥ ያን ያህል ጆሮ ገብ ነው፡ የኢትዮጵያዊነት ወግ፣ ባህሉ ፣ ሚልኩና ቀለሙ በአንድነት ጉዳይ አንድ ነው፡ የዛሬይቷ ኢትዮጵያ አዲሱ ትውልድም ከአበውና ከእመው በወረሰው የአይነኬነት ታሪክ በፊናው የሚደበዝዝ ደማቅ ታሪክ ፅፏል። በዚህም በሀገሩ ብሔራዊ ጥቅሞች ላይ የሚደራደር መሆኑን በይፋ አስመስክሯል። ብዙም ሩቅ ሳንሄድ የኤርትራ መንግስት ሀገራችንን በወረረበት ወቅት ቀፎው እንደተካ ንብ ሆ! ብሎ መውጣቱንና ወራሪወን ሃይል ድባቅ መምታቱን እንዲሁም ሀገራችን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ እንድትሰለፍ የጥርጊያ መንገድ ከሚሆመቻቹት ፕሮጀክቶች ወስጥ አንዱ የሆነወንና እነ ዶክተር ተብዬው የሚቃወሙትን ታላቁን የህዳሴወን ግድብ ዕወን ለሚድረግ በሚየቋርጥ ግለት በሁለንተናዊ ሚልኩ እያደረገ ያለወን ኢትዮጵያዊ ተግባራትን በአብነት መጥቀስ ይቻላል። እወነት እነዚህን ሃቆችና ብሔራዊ ማንነቶችን ዶክተር ብርሃኑ እንደምን ዘንግተውት ይሆን—ኢትዮጵያዊነትን ለመሸጥ ገበያ ያወጡት?... አዎ ለምላሹ ብዙም መመራመር የሚያስፈልግ አይመስለኝም— ምላሹ በእልህና በደም ፍላት ሀገርን በሸብር ተግባር የማምራት ከንቱ ሱስ ነወና፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ሰውዬው ለምን ስልጣን ተመኙ አሊያም ለምን ሰሜይን ቧጠጡ እያልኩ አይደለም፡ መመኘት መብታቸው ነው—ምኞት አይከለከልምና። ክፋቱ ግን የምኞታቸው መንገድ ከኢትዮጵያዊነት ማንነት ባፈነገጠ ሚልኩ ባንዳዊ መሆኑ ነው፡

ግና የዶክተሩ ብርሃኑ ክፋትና ሞኝነት ህዝብንና የፖለቲካ ፓርቲን አቀላቅለው ሚዳታቸው ነው፡፡ ሰወዬው ህዝብና ፓርቲ እንዲሁም ፓርቲና ሀገር አንድ ሆነው ታይተዋቸዋል፤ ተምታትቶባቸዋል፡፡ እናም ገዥውን ፓርቲ ጎዳሁ ብለው በህዝብ የዕድገት ትልም ላይ ዘመቱ፡፡ በሀገር ላይ ዘመቱ፡፡ በብሔራዊ ጥቅም ላይ ዘመቱ፡፡ …ወደድንም ጠላንም ነባራዊ እውነት ነውና ገዥው ፓርቲ የተሻለና በህዝብ የተሚረጠ ፖሊሲና ስትራቴጂ ያለው ተቃዋሚ ፓርቲ ሲመጣ ቦታውን ሊለቅ ይችላል፡፡ ሀገር ግን ዘላለማዊ ነች፡፡ የህዳሴው ግድብም ዘላለማዊና የኢትዮጵያ ህዝብ ሀብት እንጂ የገዥው ፓርቲ እሴት አይደለም፡፡ ገዥው ፓርቲ ለህዝቡ ያቀረበው ገፀ-በረከት እንጂ። እናም የዶክተሩ የሽብር ቡድን ለኢህአዴግ ጫፍን ጥላቻ ስላለው ብቻ፤ የሚኳካ ማስሎት የህዳሴውን ግድብ ስኬታማነት እንዲሁም ቢያንስ በመርህ ደረጃ የኢትዮጵያን ልማት ለሚደናቀፍ ከሚቋምጡ አንዳንድ ህልመኞች ጋር ለማሰለፍ መጃጃሉ አከሳሪ ቁማር ይመስለኛል— ራስን አስይዞ የመብላት ያህል፡፡

በእርግጥ እንደ ግንቦት 7ቱ ዶክተር ጫፍ የወጣ አይሁን እንጂ ሌሎች ለፖለቲከኝነትም የሚይመጥኑ ተቃዋሚዎች አሉን፡፡ ወይም አሉብን፡፡ በክፉ ቀን የዶክተሩ የመንፈስ ተጋሪዎች ሊባሉም ይችላሉ። በህዝብ ተቀባይነት በማጣታቸው ሳቢያ መንግስትን ያለ አግባብ የሚያማርሩ ጉደኞች፡፡ እኔ በግሌ ግን ሁሌም የማነሳቸው ጥያቄዎች አሉኝ— ‛ሀገር ወዳድ ከሆኑ ለምን በተግባር ሰርተው አያሳዩንም?፣ እንደነ ግንቦት 7 ለህዳሴው ግደብ ገንዘብ አታዋጡ ለምን ይላሉ?... የመንግስትነት ዕድል ስላለገኙ መንገድ ገንብተው ቁምነገረኛነታቸውን ልማታዊነታቸውን ማስመስከር አይችሉ ይሆናል፡፡ ቢያንስ ግን ትዕግስትን፣ ሆደ ሰፊነትንና የሀገር ፍቅርን ቢያስተምሩን ምናለበት? ራሳቸው አዱ ለሌላኛውን የአቅም ማነስ ችግር አለበት፣ እንደ ቦይ ውሃ የሚዳ ነው…ወዘተ እየተባባሉ መቻቻል ተስኗቸው ስለመቻቻል ቢደሰኩሩልን ምን ዋጋ አለው? —"ድንቄም ፖለቲከኝነት እቴ!" አሉ ጎረቤታችን እማማ ማሜ፡፡…

እስቲ የአንዳንድ ሀገር ወዳድ የልማትና የዴሞክራሲ ባህታዊ መሳይ ፖለቲከኞቻችንን ነገረ ስራ እዚህ ላይ ተውት ላድርግና ወደ "ዶክተር አኮኖሚስታችን" ልመለስ— የነገሬ ራስጌም ሆነ ግርጌ እርሳቸው ናቸውና። ሰወዬው ወዲያም አሉ ወዲህ እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም አሳፋሪ ስህተት እየፈጸሙ ነው። እኔን የገረመኝ ግን አሁንም በባንዳነት የኢትዮጵያ ህዝብ ሃብት የሆነውን ታላቁን የህዳሴ ግድብ ተፃርረው ቆመው፤ ሚሉሰው ስለ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲና ልማት ማውራታቸው ነው። ይህ የጤነነት አይመስለኝም— እብደት እንጂ፡፡

"ዶክተርዬው" በምግባራቸው ደግመው ደጋግመው ተማዘኑ፡፡ እናም ወደቁ፡፡ ወድቀውም አልተነሱም፡፡ ዛሬም ድረስ በዳዴ እየሄዱ ነው። የፈጸሙት ስህተት አንገት የሚያስደፋ በሚሆኑ ኢትዮጵያዊያንን ደግሞ ለሞትና በእነርሱ ስም ለመነገድ የሞራል ብቃት አጥተዋል፡፡ በመሆኑም እንዲህ በቅሌት ባህር ወስጥ የተጠምቀና በባንዳነት የተጨማለቀ ግለ- ታሪክ (Profile) ያለው ግለሰብና የግብረ-ሽበራ ቡድን ስለ ሀገርና ስለ ህዝብ እንደራሴ መስሎ ለማምታታት መሞከር ራስን ካለማወቅ ባለፈ ዳግም በህዝብ ዘንድ

መተፋት ነው፡፡ በቀይ ባህር ወስጥ የአቶ ኢሳያስ የሽብር ተጠሚዊው እኚሁ ግለሰብ ባለፉት 21 ዓመታት ብቻ ሀገሪቱን የዕድገት ተምሳሌት ያደረጓት እርሳቸው ይመስሉ፤ ኢህአዴግ ሀገር ለማምራት አይመጥንም ባይ ናቸው — "ዶሮ ብታልም ጥሬዋን ነው" እንዲሉ አበው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ደገሞ ግንቦት ሰባትን አይንህን ላፈር ብሎታል፡፡ ብቃቱ ማሸበር እና ተላላኪ መሆን እንጂ ሀገር ከማምራት ጋር የሚያገናኘው ጉዳይ የሌለ መሆኑን ስለሚያወቅ። አዎ!ህዝብ አስተዋይና ሚዛናዊ ነው፡፡ ህዝብ ያለው ሁሌም ትክክል ነው— ምንም እንኳን የሽብር አስተዳዳሪው ህዝብ ይሳሳታል ቢሉም፡፡

እናም "ዶክተርዬ" /እኔን ይዶክትረኝና/ ላለፉት ጊዜያት በአስመራው ሰወዬ ትከሻ ላይ ቁጭ ብለወና ለስልጣን እንዲያበቋቸው እየለሙ በአምሳያቸው እየተመሰሉ ኢህአዴግን ቢጠሉትም፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ኢህአዴግን ይበልጥ እየወደደወና እየሚጠው መጥቷል— በስራው፡፡ እናም ገዥው ፓርቲ ስላወራ ሳይሆን በተግባር ሰርቶ በማስመስሩ ከህዝቡ ጋር እጅና ጓንት መሆኑ "ጋሼ ሽብሩን" ሊያናድዳቸው ይችላል፡፡ ግና የህዝብን ይሁንታ ማግኘት የሚቻለው በእልህና ሀገርን ለድርድር በሚያቀርብ የማንነት ንግድ ላይ በነማስሚራት አይመስለኝም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ እስከሚጨረሻው ከህዝብ ጋር ሆድና ጀርባ የሚያደርግና ዋጋ የሚያስከፍል ነው፡፡ ሰወዬው "የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም" ካላሉ በስተቀር፡፡

ዶክተሩና የሽብር ቡድናቸው የተጣሉት ከኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ጋር ብቻ ባለመሆኑ እርቃናቸወን ቀርተዋል፡፡ ቀደም ሲል ባለማወቅ ለፓርቲው የገንዘብ ድጋፍ በማስባሰብ ለስራ ማስኬጃ ወደ ባንክ ሂሳብ ቁጥራቸው ይጨምሩላቸው የነበሩት የባህር ማዶ ደጋፊዎቻቸው ዛሬ ላይ ነቅተናል ብለዋቸዋል— የሰው ልጅ ሁሌም አይሸወድምና። እናም ገንዘብም ሆነ ህዝባዊ ድጋፍ የደረቁባቸው የሻዕቢያው ሎሌና የቅርቡ የካይሮው ባንዳ ቡድን፤ ይህ ባዶነቱ በወሬም ቢሆን ኢህአዴግን በኃይል ለመጣል ከሚያደርገው የህልም ሩጫ እንዳሰናከለው ሰረዳ፤ እርግጥም የሚያዘወን የሚጨብጠወን ማጣቱ አይገርምም፡፡ ሁሉንም ተመኝቶ፣ ሁሉንም አጥቷልና፡፡ ዓላማው በሽብር ተግባር ሰተት ብሎ አራት ኪሎ ቤተ – መንግስት መግባት እንጂ ሌላ ሀገራዊ ራዕይ ስለሌለው አይወድቁ አወዳደቅ ወድቋል— የሀገርን ህዳሴ ሚጋገጫ በባንዳነት ለመሸጥ በሚኬሩ፡፡

በሀገር ወስጥ መላው ኢትዮጵያው የናቃቸው ዶክተሩ በባህር ማዶም ብቻቸወን ቀርተዋል፡፡ በጥቅምና በጎጠኝነት ምክንያትም ለሁለት ተሰንጥቀዋል። ተሳስተው ያሳሳቷቸው ሁሉ ድጋፋቸወን ነፍገዋቸዋል፡፡ እናም በንዴት እጠያቸው ዱብ ብሏል፡፡ ተናድደወም አልቀሩም— ከታሪክ የሚያፋቅ ነወረኝነትን ታቅፈው የሚጨረሻ ጉዟቸው ካይሮ ወስዷቸዋል— ለሌላ ነወር፡፡ አርቆ አስተዋይነት ስላልፈጠረባቸወም እዚያም የሀገራችንን ህዝብ ሃብት ለመሸጥ ድርድር ጀምረዋል፡፡ ኢትዮጵያና ግብጽ በጠላትነት የሚፈላለጉ ማስኋቸው ተጨማሪ ኪሳራ አስመዝግበዋል፡፡ የሰወዬው ፍልስፍና እንዲያ ነው፡፡ በተሳሳተ እሳቤ አንድ እርምጃ ወደ ኢትዮጵያ ለመቅረብ በሞከሩ ቁጥር ሺህ ማይሎችን ከማንነታቸው ይርቃሉ — አጀንዳቸው በየሀገሩ እየዞሩ የጥፋት ማለከት መንፋት ነወና፡፡ ግና በየዞሩበት ሀገር የኢትዮጵያዊያንን ጥቅሞች ለስልጣን ጥማታቸው ሲሉ

በአሉባልታ ለመድፈቅ ቢሞክሩም እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም አይሳካላቸውም፤ ለሄዱበት ሀገርም የሚፈይዱት ነገር የለም—ያላቸው አቅም ወሬ ማውራት ብቻ ነወና።

ሰወዬው ግን ምናልባት ሽርፍራፊ አስተዋይነት በልቦናቸው ካለ ልብ ማለት ያለባቸው ነገር ይኖራል ባይ ነኝ። ይኸውም ወደ ግብፅም ይሂዱ አሊያም ወደ ሰሜይ ቤት ይንጎዱ ከሠላም፣ ከልማትና ከዴሞክራሲ ሥርዓት ባህል ግንባታችን ማይክሮ ሴኮንድ እንኳን ሊያዘገዩን አለመቻላቸው ነው። ምክንያቱም በግድቡ ግንባታ ዙሪያ አንድ የሆነንና ከጫፍ እስከ ጫፍ የተነቃነቀን ህዝብ እንኳንስ ባንዳ ቀርቶ ሌላም ሊፈታተነው ስለማይችል ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ሰወዬወና አሸባሪው ቡድናቸው ለባዕድ በመቆም የሀገራቸውንና የህዝባቸውን የልማት ትልም በቀን ቅዠታቸውም ቢሆን ለማደናቀፍ ዳግም እየጣሩ ናቸወና እነርሱም የእኛ፤ እኛም ሆንን ኢትዮጵያ የእነርሱ ልትሆን አንችልም፡፡ እናም ለባዕዳን በባንዳነት አድረው ከአንደም ሁለቴ ምናልባትም ሶስትና አራቴ ብለም አምስቴና ስድስቴ... ኢትዮጵያዊንን አይናችሁ ላፈር እንዳሉን ሁሉ፤ እኛም ተላላኪወን ዶክተርና የሽብር ቡድናቸውን ዓይናችሁን ላፈር ብለናችኋል፡፡...አዲዮስ ግንቦት ሰባት! . . .።